የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፳፰
አዲስ አበባ ግንቦት ፳ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

18th Year No. 28
ADDIS ABABA 28th May, 2012

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፵/፳፻፬ ዓ.ም

ለበደሌ-መቱ የመንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ …... ገጽ ፮ሺ፫፻፳፰

CONTENTS

Proclamation No.740/2012

African Development Fund Loan Agreement for Financing Bedele-Metu Road Upgrading Project Ratification Proclamation. ... Page 6328

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፵/፳፻፬

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለበደሌ-መቱ የመንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፵፩ ሚሊዮን ፷ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት (አርባ አንድ ሚሊዮን ስልሳ ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.አ.አ. ፌብርዋሪ ፫ ቀን ፪ሺ፲፪ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፴ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለበደሌ-መቱ የመንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፵/፳፻፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION No. 740/2012.

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND**

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of forty one million sixty thousand units of account (UA 41,060,000) for financing Bedele-Metu Road Upgrading Project was signed in Addis Ababa on the 3rd day of February 2012;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 8th day of May 2012;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "African Development Fund Loan Agreement for Financing Bedele-Metu Road Upgrading Project Ratification Proclamation No.740/2012".

፪. **የስምምነቱ መጽደቅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ፌብርዋሪ ፫ ቀን ፪ሺ፲፪ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር 2100150025495 የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፫. **የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፵፩ ሚሊዮን ፷ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት (አርባ አንድ ሚሊዮን ስልሳ ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፳ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም**

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2. **Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement No.2100150025495 signed in Addis Ababa on the 3rd day of February 2012, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund is hereby ratified.

3. **Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of forty one million sixty thousand units of account (UA 41,060,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 28th day of May, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**